# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ኤፌሶን ሰዎች

## ጥናት 9 (3፣1-13) ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ

### የአሕዛብ ሐዋርያ ቁ. 1-2

- በኤፌሶን ጥናት መግቢያችን ላይ እንደገለጽነው በ60 ዓ.ም. ገደማ በሮም እስር ላይ እያለ ይህን ደብዳቤ እንደጻፈው ይታመናል:: ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ማለትም ጌታን ታዝዞ ለአሕዛብ ወንጌልን በመስበኩ ምክንያት እንደታሰረ ነው በዚህ ክፍል ጳውሎስ እየገለጸ ያለው:: የጳውሎስ ጥሪ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን እንደሆነ በተለያዩ ቦታዎች ተገልጿል ሮሜ 15፣15-16 ገላ 2፣7-8:: እዚህ ላይ ሳንጠቅስ የማናልፈው፣ በጣም የሚገርም ነገር አለ:: ይሄውም እንደሰው ስናስበው ጳውሎስ የአሕዛብ ሐዋርያ ከሚሆን ይልቅ የአይሁድ ሐዋርያ ቢሆን እጅግ የበለጠ ውጤት የሚያመጣ ይመስላል:: ምክንያቱም ጳውሎስ በስምንተኛው ቀን የተገረዘ፣ ከእስራኤል ትውልድ የሆነ፣ ከብንያም ወገን፣ ከዕብራዊም ዕብራዊ ነው:: ሕግንም በማወቅ ቢሆን ፈሪሳዊ ነበር፣ ለአይሁዲነቱ ቀንቶ ቤተክርስቲያንን አሳዳጅ የነበረ፣ በሕግ በሚገኘው ጽድቅ ያለነቀፋ የነበረ ዋና አይሁዳዊ ነበር ፊል 3፣5-7:: ከላይ ስለ እርሱ የተዘረዘሩትን ነገሮች አይሁድ ስለሚያውቁ፣ እንደሰው ስናስበው ጳውሎስ የአይሁድ አገልጋይ ቢሆን ትልቅ ውጤት የሚያመጣ ይመስላል:: በየሐዋ. 22፣17-21 ላይ እንደተጻፈው ጳውሎስም ራሱ የአይሁድ አገልጋይ ቢሆን ውጤታማ እንደሚሆን ያስብ ነበር:: ጌታ ግን "ፍጠን ከኢየሩሳሌምም ቶሎ ውጣ፣ ስለ እኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህም" አለው የሐዋ 22፣18:: የጌታ ጥሪ እንደ ሰው በሎጂክ ስላይደለ፣ ጌታ ወደ አሕዛብ ላከው:: የእግዚአብሔር ጥሪ ከሰው ሃሳብ የተለየ ነውና:: ይህም በዘመናችን በብዙ ቦታዎች ተደጋግሞ ከሚታየው ተመሳሳይና አንድ አይነት ጥሪ እጅግ የተለየ ነው::

- መጋቢነት:- መጋቢነት/stewardship የሚለው ቃል ኦርጂናል ትርጉሙ ምግብ መመገብ ከሚለው ጨርሶ የተለየ ወይም ሰፋ ያለ ነው:: የግሪኩ ሌክሲኮን ቃሉን እንደሚከተለው ይፈታዋል:- The management of a household or of household affairs; specifically, the management, oversight, administration, of others' property; the office of a manager or overseer, stewardship. ይህም ማለት የሌላ ሰውን ንብረት ወይም የሌላ ሰውን የቤቱን ጉዳይ የሚያስተዳድርና በባላይ የሚቆጣጠር ወይም ኃላፊ ማለት ነው:: በሉቃ 16፣1-9 እና በገላ 4፣1-2 ያሉት ክፍሎች የዚህን ቃል ምንነት በትክክል እንድንረዳ ያግዙናል:: በሮሜ 16፣23 ላይ ይህ ቃል ራሱ የከተማዋን ንብረት ተቆጣጣሪ/treasurer ሲያመለክት እናያለን:: ስለዚህ ቃሉ ሊያመለክት የሚፈልገው ዋናው ነገር፣ የራስን ሳይሆን የሌሎችን ንብረት በአግባብ ማስተዳደርን ነው:: ይህንን ቃል በመንፈሳዊ አገልግሎት ስንመለከተው ደግሞ እግዚአብሔር ለአገልግሎት የሰጣቸውን የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ጸጋ የሚያስተዳድሩትን ወይም እግዚአብሔር በሰጣቸው መንፈሳዊ ጸጋ ሰዎችን የሚያገለግሉትን ሁሉ የሚያመለክት ነው:: አደራ የተባሉትን የእግዚአብሔርን የአገልግሎት ጸጋ/ንብረት እንደ መጋቢ/አስተዳዳሪ/manager በታማኝነት የሚያስተዳድሩ ወይም በአግባብና በጥበብ በተገቢው ጊዜና ቦታ ጥቅም ላይ የሚያውሉትን የሚገልጽ ነው 1ቆሮ 4፣1-2 1ጴጥ 4፣10:: ጳውሎስም እንግዲህ የራሱን እውቀት ሳይሆን እግዚአብሔር ለአሕዛብ ጥቅም ሲል የሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ/ንብረት እንዲያስተዳድር የተሾመ እንደሆነ ነው የሚገልጸው::

### የተገለጠለት ምስጢር ቁ. 3-6

ጳውሎስ አንድ ምስጢር እግዚአብሔር እንደገለጸለት በዚህ ክፍል ይናገራል:: ከዚህ ክፍል በፊት ያሉትን የመልዕክቱን ክፍሎች የሚያነብ ሰውም ምን ያህል ይህ ምስጢር እንደተገለጠለት ሊረዳ እንደሚችል ነው ጳውሎስ የሚገልጸው::

- የምስጢሩ ምንነት:- ምስጢሩን በአጭር ቃል እንዲህ ሲል ይገልጸዋል:- "አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ (joint-heirs)፣ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ (joint-body)፣ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ (joint-sharers)" ቁ. 5-6:: አሕዛብ አንድ ቀን እንደሚባረኩ የብሉይ ኪዳን ነብያትም ከአብርሃም ጀምሮ የተገለጠላቸው ነገር ነበር:: አሁን ለሐዋርያትና ለነብያት የተገለጠውና በሌሎች ትውልዶች ያልተገለጠው ነገር፣ አሕዛብ ከመባረክም አልፈው፣ ለአይሁድ የተሰጠውን የተስፋ ቃል እኩል ተካፋይ መሆናቸው ነው:: እንዲሁ በርቀት የሚባረኩ ሳይሆኑ፣ እንደ አይሁድ እኩል የእግዚአብሔር ልጆችና ወራሾች፣ የአዲሱ አካል (የቤተክርስቲያን) እኩል ብልቶችና የተሰጠውን የተስፋ ቃል በእኩል ደረጃ ተካፋዮች መሆናቸው ነው:: ለዚህም ነው የአይሁድ ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በአሕዛብ ላይ ሲወርድ የተገረሙት የሐዋ 10፣44-46:: በክርስቶስ ካለ ድነት ጋር አብሮ የተገለጠው ምስጢር እንግዲህ የቤተክርስቲያን ምስጢር ነው:: ቤተክርስቲያን አይሁድና አሕዛብ አንድ

የሚሆኑበት አዲስ ሕዝብ ወይም አዲስ አካል ናት፡፡

- ሐዋርያትና ነብያት፡- በዚህ ክፍል ነብያት ተብለው የተጠሩት የአዲስ ኪዳን ነብያት እንደሆኑ ግልጽ ነው፡፡ "...ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነብያት በመንፈስ አሁን እንደተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም፡፡" ቁ. 5-6፡፡ ሐዋርያትና ነብያት ከሌሎቹ አገልጋዮች የሚለያቸው ዋናው መለያ፣ የክርስቶስ ምስጢር እጅግ የተገለጠላቸው መሆኑ ነው፡፡ ከማናቸውም አይነት መገለጥ ሁሉ የሚበልጠው መገለጥ የክርስቶስ ምስጢር መገለጥ ነውና፡፡ የብሉይም እንኳን ነብያት ትልቁ መልዕክትና መገለጥ ክርስቶስ ነው ዮሐ 5፣39 ሉቃ 24፣25-27፡፡ ስለዚህም በአዲስ ኪዳን፣ ነብያት ከትንቢት ተናጋሪዎች የተለዩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም የነብያት ትልቁ መለያ፣ የክርስቶስ ምስጢር መገለጥ ነውና፡፡ ትንቢትንም የሚናገር ሁሉ ነብይ አይደለም፡፡ ስለ ነብያት አገልግሎት በምዕራፍ 4 በስፋት ስለምንመለከት፣ ለጊዜው ይሄ ይበቃናል፡፡
- በመንፈስ የሆነ መገለጥ፡- ጳውሎስ ስለመገለጥ ሲናገር በትምህርት ወይም በራስ ጥረት ወይም በአዕምሮ ብስለት ስለሚገኝ ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲያው በመንፈሱ ስለሚገልጠው ነገር ነው፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ የእግዚአብሔር ምስጢር ሊገለጥ አይችልምና 1ቆሮ 2፣10-16፡፡

## የወንጌል አገልጋይ ቁ. 7-9

- ሀ) አገልጋይ/servant/minister:- የዚህ ጥሬ ቃል ትርጉሙ፣ የሌላውን ወይም የበላዩን ትዕዛዝ የሚፈጽም አገልጋይ/ባለሟል/አሽከር ማለት ነው፡፡ የቃሉን መሠረታዊ ትርጉም ለመረዳት፣ ቃሉ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰባቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች ማየቱ ይረዳናል፡፡

  1. ጠቃሚ ሎሌ/ባለሟል ማቴ 20፣25-28፡- እዚህ ላይ ሌሎችን በመጥቀም ላይ ያተኮረ ወይም ለሌሎች ደህንነት/ምቾት/በጎነት/welfare የሚተጋ ማለት ነው፡፡ የሌሎችን ጥቅም ከራሱ በፊት የሚያስቀድም፡፡ መሆን ካለበትም ለሌሎች ጥቅም ሲል ነፍሱን እንኳን መሥዋዕት የሚያደርግ፡፡ "የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፡፡" ማቴ 20፣28፡፡ አገልጋይ ጠቃሚ ነው፡፡ አገልጋይ አገልጋይነቱ የሚታወቀው በጠቃሚነቱ ነው፡፡ ባለሟል ወይም ሎሌ ሌሎችን መጥቀም ካቆመ አገልጋይነቱን አቆመ ማለት ነው፡፡ በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ እርሱ የሚያገኘው ጥቅም ምንም ሚና አይጫወትም፡፡ ወሳኙ ነገር ሌሎች ከአገልጋይ ወይም ከባለሟል ማግኘት የሚገባቸው ጥቅም ብቻ ነው፡፡ ከባለሟል ችግር አይጠበቅም፡፡ የንጉስ ባለሟል ወይም አገልጋይ የሚቀጠረው ጥቅም እንዲሰጥ፣ ሌሎችን እንዲረዳና ሌሎቹ መልካም እንዲሆንላቸው እንጂ፣ ችግር እንዲሆንባቸው አይደለም፡፡ አገልጋይ ለሌሎች ጠቃሚ ዕቃ መሆኑን አቁሞ ራሱ ችግር መሆን ከጀመረ፣ አገልጋይነቱን ትልቅ የጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡
  2. ምግብ አሳላፊ/አስተናጋጅ/ማዕድ አቅራቢ/waiter ዮሐ 2፣5/9፡- ይህ አገልጋይ የሚለው ቃል ለምግብ አሳላፊዎችና ለማዕድ አስተናጋጆችም የተሰጠ ስም ነበር፡፡ ይሄም በማዕድ የተቀመጡት እንዲበሉ፣ እንዲጠጡ፣ መልካም እንዲሆንላቸው እነርሱ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማቅረብ ነው፡፡ በገሊላ ቃና በተደረገው ሠርግ ላይ የወይን ጠጅ ማለቁን ያወቁና ጌታ እንዳዘዛቸው ጋኖችን ውሃ ይሞሉ የነበሩ አገልጋዮች/አሳዳሪዎች/አሳላፊዎች ናቸው፡፡ በማዕድ የተቀመጡት ስለ ነበረው ችግርና ጭንቀት የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡ በማዕድ የተቀመጡት ጠግበው እንዲበሉና እንዲጠጡ በድብቅ ሲለፉና ሲተጉ የነበሩት አገልጋዮች ናቸው፡፡ የማዕድ አስተናጋጅ ወይም አሳላፊ ዋናው ሥራው በማዕድ የተቀመጡት ምንም እንዳይጎድላቸው ማድረግ ነው፡፡ እርሱ ግን ዋና አክተር ወይም ዋና ተዋናይ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሆቴል ቤትም ይሁን ባገራችን ሰው ቤት ተጋብዘን በማዕድ ስንመገብ፣ ከምግቡ ወይም ከግብዣው በኋላ የሆቴሉ አስተናጋጅም ይሁን የተጋበዝንበት ቤት ሰራተኛ ምን አይነት ሰዎች እንደነበሩና ምን አይነት መልክ እንደነበራቸው እንኳን ብዙ ጊዜ ልብ አንልም፡፡ የማዕድ አሳላፊዎች ብዙ ጊዜ እየታዩ የማይታዩ ናቸው፡፡ ምግብ ባቀረቡ ቁጥር ትልቅ መለከት አይነፉም ወይም የራሳቸውን ማንነት ለማስተዋወቅ አይጥሩም፡፡ የሚያስፈልገንን ይዘውልን በመጡ ቁጥር ከመቀመጫችን እየተነሳን በአክብሮት አንቀበላቸውም፡፡ አገልግለውም ሲጨርሱ ምስጋናና ሙገሳን አይጠብቁም፡፡ ነገር ግን እነርሱ ዋና አክተር ሳይሆኑ ትልቅ ጥቅም ሰጥተው ያልፋሉ፡፡ የማዕድ አገልጋይነት እንግዲህ ለራስ ልዩ ክብርና ምስጋናን ሳያገኙና ዋና ተዋናይና አክተር ሳይሆኑ፣ እየታዩ ሳይታዩ ሌሎችን ጠቅሞ ማለፍ ነው፡፡
  3. ዲያቆን፡- በዚህ ክፍል አገልጋይ የሚለው ቃል በግሪኩ diakonos የሚለው ቃል ነው፡፡ ይህም በአዲስ ኪዳን ዲያቆናትን ወይም ድቁናን ለማመልከትም ያገለገለ ቃል ነው፡፡ የድቁና አገልግሎት ዋና ማዕከል፣ የተቸገሩትን ወይም ድሆችን፣ መበለቶችን፣ በሽተኞችን ወዘተ በሚያስፈልጋቸው መርዳት ነው፡፡ በየሐዋ 6፣1-2 ላይ የተጠቀሱትም መበለቶች እውነተኛ ችግረኞች እንጂ፣ በቤተክርስቲያን የሻይ ፕሮግራም ላይ በደንብ ያልተስተናገዱ መበለቶችን ለመጥቀስ አይደለም፡፡ ድቁና ሌሎች በጎ ይሆንላቸው ዘንድ፣ እነርሱን ለመርዳት የሚደረገን ማንኛውንም በጎ አድራጎት ወይም የረድኤት አገልግሎት ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

4. ታናሽ:- የአገልጋይነት አንዱ ባሕርይ ታናሽነት ነው:: ከላይ ያየናቸው ባለሟልም ይሁን የማዕድ አሳላፊ ሁለቱም ሥራዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ዝቅተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ሥራዎች ነበሩ:: ስለዚህም ዝቅ ማለትን፣ ከሌሎች ማነስንና መዋረድን የሚያሳዩ ናቸው:: እንዲያውም ጌታ፣ አገልጋይነት ትልቅ የመሆን ተቃራኒ እንደሆነ ነው የሚገልጸው "...የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው (exercise lordship over them) ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ (exercise authority over them) ታውቃላችሁ:: በእናንተስ እንዲህ አይደለም፣ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፣ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን" ማቴ 20፣25-27:: ስለዚህ እንደ ጌታ አገላለጽ አገልጋይ መሆን ማለት የታላቅ ተቃራኒ ወይም ታናሽ መሆን ማለት ነው:: ስልጣንን በሌሎች ላይ መለማመድ ወይም ሌሎችን ማዘዝና መግዛት ሳይሆን፣ ሌሎችን ዝቅ ብሎ መጥቀም ማለት ነው:: ልክ ታናሽ ሕጻን ልጅ ራሱን እያዋረደና እየታዘዘ እንደሚጠቅም እንጂ ሌሎችን እንደማይገዛ አገልጋይነትም እንዲሁ ነው ማቴ 18፣4 ሉቃ 9፣46-48:: በጌታ ቤት እውነተኛ ስልጣን እንደ አሕዛብ አለቆች ብዙ በማዘዝና ብዙ በመቆጣጠር የሚታይ ሳይሆን በዙ በመጥቀም የሚገለጥ ነው:: በማዕድ ስለሚያስተናግዱትም ጌታ ሲናገር፣ በማዕድ ማስተናገድ ወይም ማዕድ አሳላፊነት ትንሽነትንና መዋረድን የሚያመለክት እንጂ የበላይነትን ወይም ገዢነትን አያሳይም:: "በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ::" ሉቃ 22፣27:: ስለዚህ በማዕድ ማገልገል አሽከርነትን ያመለክታል እንጂ ክብርን አይደለም:: ስለዚህ አገልጋይነት ራሱ የትልቅነት ተቃራኒ ነው እንጂ የበላይ መሆንን አያመለክትም::

- ማጠቃለያ:- ጳውሎስ እንግዲህ የወንጌል አገልጋይ ሆንሁ፣ ሲል ትልቅ ገዢና ተቆጣጣሪ ነኝ ማለቱ አይደለም ወይም ይሄን ሲል ስለ ልዩ ገዢነት ወይም የክብር ስፍራ ሳይሆን የሚናገረው፣ ለሌሎች ጥቅምና በጎነት በወንጌል የምተጋ ባለሟል ወይም አሽከርና አሳላፊ ሆንኩኝ ማለቱ ነው::

- ለ) እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ መጠን የሆነ አገልግሎት
  - ጳውሎስ አገልግሎቱ "እንደ ኃይሉ ሥራ" እና "እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ መጠን" እንደሆነ ይናገራል:: ጳውሎስ እንዲህ የወንጌል አገልጋይ እንዲሆን ያደረገውና ያበቃው የእግዚአብሔር ኃይልና ጸጋ እንጂ የራሱ ጥረት እንዳልሆነ ለማመልከት ነው:: አገልግሎት የእግዚአብሔር የምሕረቱና የጸጋ/የነጻ ስጦታው ምልክት ነው እንጂ፣ የሰው ማንነት ወይም የሰው ጥረት ምልክት አይደለም:: ስለዚህ የአገልግሎት ብቃትንም ይሁን ትጋትን የሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ነው ጳውሎስ በመልእክቶቹ የሚገልጸው 2ቆሮ 3፣5 1ቆሮ 15፣10::

- ሐ) የአገልግሎቱ ምንነት
  - ለጳውሎስ የተሰጠው አገልግሎት "ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስ ባለጠግነት" ለአሕዛብ መስበክና በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰውሮ የነበረውን ምስጢር መግለጥና ማስታወቅ ነው:: "ፍለጋ የሌለው" የሚለው ቃል፣ unsearchable ወይም ተመርምሮ የማያልቅ እጅግ ብዙ ወይም ወሰን የሌለው ወይም ታውቆ የማይጨረስ ለማለት ነው:: ይህም የክርስቶስ ባለጠግነት ገደብ የሌለው ወይም ተመርምሮ የማያልቅ እንደሆነ ለማሳየት ነው:: ጳውሎስ የተገለጠለትን መገለጥ ብቻ ሳይሆን፣ የአገልግሎቱንም አላማና ምንነት ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው::

- መ) ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ የማንስ
  - ጳውሎስ ከላይ የተገለጠለትን መገለጥ ታላቅነት ገልጿል:: ይህም መገለጥ በሌሎች ትውልዶች እንኳን ያልተገለጠ መገለጥ እና እጅግ ድንቅ የሆነ መገለጥ ነው:: በጣም የሚገርመው ግን፣ ጳውሎስ ከተገለጠለት መገለጥ ታላቅነት ጋር አብሮ የሚጠቅሰው ደግሞ የራሱን ታላቅነት ሳይሆን የራሱን ታናሽነት ነው:: የመገለጥ ትልቅነትና የእውቀት ብዛት እንደሚያስታብይ ራሱ ጳውሎስ በሌሎች መልእክቶቹ ጠቅሷል 2ቆሮ 12፣7 1ቆሮ 8፣1:: ከመገለጥና ከእውቀት ብዛት ሰዎች ስለራሳቸው ያላቸው አስተያየትም ከፍ ይላል:: ጳውሎስ ግን በመጀመሪያ ምን አይነት ሰው እንደነበረና እግዚአብሔርም ከምን ሁኔታ እንዳወጣው ያልረሳ ሰው ነው:: "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፣ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፣ ስለዚህ ግን የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ፣ ምሕረትን አገኘሁ::" 1ጢሞ 1፣15-16:: "ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ:: እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፣ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ..." 1ቆሮ 15፣8-10:: ምንም እንኳን ለጳውሎስ የተገለጠለት መገለጥ ታላቅ ቢሆንም፣ ራሱን ግን ከአማኞችና ከሐዋርያት ጋር ሲያለካካ "ከቅዱሳ ሁሉ ይልቅ የማንስ" እንዲሁም "ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ" የሚሉትን ስንኞች ነው የሚጠቀመው:: ይህም ትህትናና ራስን ከሌሎች ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ የእውነተኛ የክርስቶስ አገልጋዮች ትልቁ ምልክትና መለዮ ነው "...ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቁጠር" ፊልጵ 2፣3::

### የእግዚአብሔር የዘላለም አሳብ ቁ. 10-11

- የእግዚአብሔር የዘላለም አሳብ፣ በሰማይና በምድር ያሉትን በክርስቶስ አገዛዝ ውስጥ መጠቅለል እንደሆነ በጥናት 3 ላይ ተመልክተናል:: በዚህ ክፍል ደግሞ፣ የዚሁ አሳቡ አንዱ ክፍል "ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ" እንደሆነ ተጠቅሷል ቁ. 10:: "ብዙ ልዩ ልዩ" ወይም manifold የሚለው ቃል የቁጥር ብዛትንና የአይነት ብዛትን የሚያመለክት ነው (many and various):: በባሕር ውስጥ ያሉትን ዓሣዎች ወይም በምድር ላይ ያሉትን አእዋፋት እንደ ምሳሌ ብንወስድ በአይነትም ብዙ፣ በቁጥርም ደግሞ እንዲሁ ብዙ ናቸው:: የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ የተለያየና እጅግ ብዙ እንደሆነ ለመግለጽ ጳውሎስ የተጠቀመበት ቃል ነው:: የእግዚአብሔር አንዱ የዘላለም አሳብ እንግዲህ ይህን ጥበብ በቤተክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ማሳወቅ ነው:: ይህም ማለት እግዚአብሔር ራሱ በቤተክርስቲያን የሚገልጠውን ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ያሉት አለቆችና ሥልጣናት እንደሚያዩትና እንዲያስተውሉት ለመግለጽ ነው:: ምክንያቱም ቤተክርስቲያን በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት የእግዚአብሔርን ጥበብ የመስበክ ኃላፊነትም ይሁን ችሎታው አልተሰጣትም:: እዚህ ላይ ግን አብሮ የሚነሳው ጥያቄ፣ ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ ወደቁት የክፉት ሠራዊትና የጨለማ ኃይላት ነው ወይስ ስለ ቅዱሳን መላእክት ነው የሚል ነው? ሁለቱንም የሚደግፉ ትርጓሜዎች በመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይሰጣሉ:: ሆኖም ግን እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት የተሰወረውንና የከበረ፣ ብዙ ልዩ ልዩ ጥበቡን እንዴት ለክፉት ሠራዊት ለመግለጥ ይወዳል? ለጌታ ለቀረቡት በተለይም ለቅዱሳን ሐዋርያቱና ነብያቱ የገለጠውና የሚገልጠው ጥበብ፣ ለማያምኑ ሰዎች እንኳ ጨርሶ ሊገለጥ የማይችለው ጥበቡ፣ እንዴት ለክፉት ሠራዊት ሊገለጥ ይችላል? የሚሉት ጥያቄዎች፣ ምናልባት በዚህ ክፍል የሚናገረው ስለ ቅዱሳን መላእክት ሳይሆን አይቀርም የሚለው አተረጓጎም ይበልጥ ሚዛን እንዲደፋ ያደርገዋል::

### ድፍረትና መግባት ቁ. 12

- በዚህ ክፍል የተጠቀሰው መግባት ልክ ባለፈው ምዕራፍ በኤፌ 2፣18 ላይ "በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ <u>ወደ አብ መግባት</u> አለንና" ተብሎ እንደ ተጠቀሰው አይነት፣ አንድ አይነት የግሪክ ቃል ነው:: ይህም ቃል ወደ እግዚአብሔር ፊት መምጣትን፣ መጠጋትን፣ መቅረብን የሚያመለክት ነው:: እኛም በክርስቶስ ሥራ ወይም "በእርሱ ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን/በእርግጠኝነት/confidence ድፍረትና/boldness መግባት/በፊቱ መቅረብ/access በእርሱ/በጌታ አለን::":: ያለምንም የሰውም ይሁን የመላእክት አማላጅነት፣ ያለ ፍርሃት፣ ነገር ግን በድፍረትና በእርግጠኝነት ወደ እግዚአብሔር የመምጣትና ወደፊቱም የመቅረብ እድል ለእኛ በክርስቶስ ተሰጥቶናል:: እርግጠኝነታችንና ድፍረታችን ክርስቶስ ለእኛ በሠራው ሥራ ምክንያት ነው እንጂ ከማንነታችን አይደለም:: ስለዚህ ሁሉን ወደሚችል አባታችን ፊት በመንፈስ ቀርበን ጥያቄያችንን ለእግዚአብሔር ለማሰማት እንችላለን:: ስለዚህም ጳውሎስ ይህን ከጻፈ ብኋላ ወዲያው ከቁ. 14 ጀምሮ በአብ ፊት ተንበርክኮ ስለሚጸልየው ጸሎት ነው የሚናገረው:: የነገሥታት ንጉሥ ወደ ሆነውና ሁሉን እንደ ፈቃዱ ሊለውጥ ወደሚችለው አባታችን ፊት የመቅረብ እድል እንዴት ታላቅ ነው! ይህ ታላላቅ የምድር ባለሥልጣናት ካላቸው ሥልጣን ሁሉ የበለጠ እድል ነው:: አስቴር በሕዝቡዋ ላይ ያንዣበበውን የመከራ ጥላ ለማግለል ያስቻላት አንድ ነገር ብቻ ነው:: ይህም ከሃማ ሥልጣን በላይ ባለሥልጣን ወደ ሆነው ወደ ንጉሡ ፊት መቅረብ! አስቴ 4፣15-16 አስቴ 5፣1-2:: ወደ አብ የመግባት መብት፣ ቢገባን ብዙ እንቆቅልሾቻችንን መፍታት የሚያስችለን ትልቅ እድል ነው::

### ክቡር መከራ ቁ. 13

- ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ከዘረዘረ በኋላ በዚህ ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ምክንያት እንደታሰረ ይገልጻል:: "ስለ እናንተ ስላለ መከራዬ" ይላል:: ስለዚህ መከራውና እሥራቱ የመጣው ስለ ክፉ ሥራው ሳይሆን ስለ ወንጌል ስለሆነ፣ የሚያሳፍር እሥር ሳይሆን እንዲያውም ሊመኩበት የሚገባ የክብር መከራ እንደሆነ ነው የሚገልጸው:: የወንጌል ነገር ካልገባን መከራ በእርግጥ ተስፋ የሚያስቆርጥና በዚህ ክፍል እንደተገለጠው የሚያታክት/to be faint ነው ማቴ 13፣20-21:: ስለዚህ በእርሱ መከራ እንዳይዝሉ፣ እንዳይታክቱና ተስፋ እንዳይቆርጡ ነገር ግን ይልቁን ክብር እንደሆነ አውቀው ወደፊት እንዲበረቱ ነው የሚያሳስባቸው:: "...ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው፣ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው:: እነርሱም <u>ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ</u> ከሸንጎው ፊት <u>ደስ እያላቸው ወጡ</u>፣ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ <u>ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር</u>::" የሐዋ 5፣40-42::